# የሕዝባዊ እምቢተኝነት ስልት ለኢትዮጵያ

# CIVIL DISOBEDIENCE STRATEGY FOR ETHIOPIA

## ከአባ ባሕርይ መድረክ

**ነሃሴ 29, 2017 ዓ. ም | September 4, 2025**

## ሀ. መግቢያ

የአባ ባሕርይ መድረክ[1] ይህን የነውጥ-አልባ ሕዝባዊ እምቢተኝነት የትግል ስልት[2] ያዘጋጀው ኢትዮጵያውያን በሰላማዊ መንገድ በስፋት የሚያደርጉትን ሕዝባዊ እምቢተኝነት ዉጤታማ እንዲሆንና ዜጎች ከተደቀነባቸው የህልዉና አደጋ እንዲወጡ፣ ኢትዮጵያ አገራችንም ከገባችበት የፖለቲካ፣ ማህበራዊና የኢኪኖሚ ምስቅልቅል እንድትወጣና ፍትህና የህግ የበላይነት የሰፈነባት አገር እንድትሆን ለማድረግ ነው። በዚህ ስትራቴጂ ከተለያዩ አገራትና ካለፈው የአገራችን ህዝባዊ እምቢተኝነት ታሪክ ምን እንማራለን፣ የሕዝባዊ እምቢተኝነቱ አደረጃጀት፣ ግብና ዝርዝር ስልቶች ተካተዋል።

ጨፍጫፊ፣ ከፋፋይ፣ አፋኝና በነገድ ስም የሚገዛ አምባገነናዊ አገዛዝ በሰፈነባት፣ በህገመንገስት የተደገፈ ቋንቋን/ነገድን መሰረት ያደረገ የዘውግ አደረጃጀትና፣ ክፍፍል ስር በሰደደባት ኢትዮጵያ የመጥፋት አደጋ ላይ የወደቁና የዘር[3] ማጥፋት እየተፈጸመባቸው ያሉ ዜጎች ህልውናቸዉን ለማስከበር የተለያየ የትግል ስልት እንዲከተሉ ይገደዳሉ። ዘላቂ መፍትሄ ለማምጣት የሕዝባዊ እምቢተኝነት ስትራቴጂ ነድፎ መንቀሳቀስ አንዱ ስልት ነው። ይህም ሕዝባዊ እምቢተኝነት ሲታሰብ ፣ የአገሪቱንና የቀጠናውን ተለዋዋጭ ሁኔታና ሥጋቱንና ሊያስከትል የሚችለውን ውጤት በጥንቃቄ ማጤንን ይጠይቃል።

የሕዝባዊ እምቢተኝነቱ ህወሃት ስልጣን ከያዘ ጀምሮ የተፈጠረውን ቋንቋን/ነገድን መሰረት ያደረገ የዘውግ ልዩነት በማጥበብ በህዝብ መካከል መቀራረብና አንድነትን በሚያጎለብት፣ የርስ በርስ ግጭትን በማስቀረት እና በአገዛዙ ላይ ከፍተኛ የተባባረ አስገዳጅ ጫና በሚፈጥር መልኩ መዋቀር አለበት። ከሁሉም በላይ ደግሞ የሚፈጠረውን ክፍተት ተጠቅመዉ ባልተጠበቀ ሁኔታ ወደ ስልጣን ኮርቻ ሊወጡ የሚችሉና የነበረውን ዘረኛ አገዛዝ ስርዓት በሌላ መሪ ሊያስቀጥሉ የሚችሉትን ሁሉ በንቃት መጠበቅ ይገባል። ዜጎች ተደራጅተው በስፋትና በስልት የሚያደርጉት ህዝባዊ እምቢተኘነት ለኢትዮጵያ ስርዓታዊ ለዉጥና ዘላቂ

---

[1] **የአባ ባሕርይ መድረክ** ከቡድን ፖለቲካ ገለልተኛ የሆኑ ምሁራንና ባለሚያዎች ያቋቋሙት ሲሆን ዓላማውም በአማራው ላይ የተደቀነውን የኅልውና አደጋና ሰቆቃ ለመታደግና እንዲሁም በኢትዮጵያ ሃገረ-መንግስት ላይ ለተደረገው የከፋፋዮች ጥልፊት መፍትሄዎችን በጥናት በማፍለቅ ምክረ-ሃሳብ ለመለገስ ነው። ሰነዶቻችንን ለማግኘት ድረ-ገጻችንን እየተመላለሱ ይጎብኙ፡- **www.abbabahrey.org.**

[2] ለሰፊ ግንዛቤ ይህን መጽሃፍ ይመለከቱ፡-ጂን ***ሻርፕ--ከአምባገነን አገዛዝ ወደ ዲሞክራሲ*** ወድ አማርኛ በ2002 [Gene Sharp, From Dictatorship to Democracy, 1973.]

[3] ዘር፣ ዘውግ ፣ ጎሳ፣ ነገድ፣ ብሄረሰብ፣ የሚሉት ቃላት በኢትዮጵያ ፖለቲካ ትርጉማቸው ግልጽ አይደሉም፡፡ በዚህ ጽሁፍ 'ዘር' 'ዘውግ' 'ጎሳ' የሚሉት ቃላት በሚናገሩት ቋንቋ ወይንም በትዉልድ ሃረጋቸው እንደ አንድ ቡድን ተለይተው የሚታዩትን ሰዎች ለማለት ነው፡፡ ዘረኛ ማለት ዜጎችን በሚናገሩት ቋንቋ ወይንም በትዉልድ ሃረጋቸው ለይተው የሚያገሉትን ወይንም የሚያጠቁትን ለማመላከት ነው፡፡

መፍትሄ ለማምጣት ይረዳል። ዜጎች በአገራቸው ጉዳይ በንቃት ካልተሳተፉና የአገራቸውን ጉዳይ የተለያየ ስልት እየያዙ በተደጋጋሚ ለሚመጡ ለተወሰኑ አፈጮሌዎችና ህዝብን ከፋፋዮች ከተወ፣ አሁንም ጉዳዩ ጉልቻ መቀያየርና አረመኔዉን ከፋፋይ ስርዓት በሌላ መሪ ማስቀጠል ይሆናል። ኢትዮጵያ ከዚህ ከተጫናት መከራና ስጋት እንድትወጣና ስርዓታዊና መዋቅራዊ ለዉጥ እንዲመጣ፣ ሁሉም ሰው ለህዝባዊ እምቢተኝነቱ አስተዋጾ ሊያደርግ ይገባል። ለዚህም ይኽ አጠቃላይ የሕዝባዊ እምቢተኝነት ስትራቴጂ አስፈልጓል። የሕዝባዊ እምቢተኝነቱን የሚመራው ማዕከል/ስብስብ/ እንደ ተጨባጭ ሁኔታው ይህን ስትራቴጂ ሊያሻሽለውና ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ/ታክቲክ/ ሊያወጣለት ይገባል።

## ለ. ከታሪክ የምንማራቸው

በተለያዩ የአለም አገራት የተደረጉ ህዝባዊ እምቢተኝነቶችን ለኢትዮጵያ ሁኔታ ከሚሰጡት ትምህርት አንጻር በመደሳስ እንጀምራለን። ቀጥሎም ከዘውዱ ስርዓት ጀምሮ ወጣቶችና የባለሙያ ማሕበራት ከተካፈሉባቸው ሕዝባዊ ንቅናቄዎች የተገኙትን ትምህርቶች እንገመግማለን።

### ፩) በተለያዩ አገሮች የተካሄዱ ህዝባዊ እምቢተኝነት ምን ያስተምሩናል?

በአለማችን ውጤታማ የሆኑ የተለያዩ ህዝባዊ እምቢተኝነቶች ተካሄደዋል። ከነዚህም ዉስጥ ማሃትማ ጋንዲ የተመራው የህንዱ፣ በዩናይትድ ስቴትስ በነ ሮዛ ፓርክስ እና ዶ/ር ማርቲን ሉትር ኪንግ የተመራው በመንገመሪ የህዝብ ማማለሻ አዉቶብስ ላይ የተደረገ ያለመሳፈር አመጽ፣ በደቡብ አፍሪካ በአፍሪካ ብሄራዊ ኮንግረስ እና በኔልሰን ማንደላ የተመራው የጸረ-አፓርታይድ ህግ እንቅስቃሴ፣ በቀድሞዋ ምስራቅ ጀርመን ላይፐዚግ ከተማ በቤተክርስቲያንና ዜጎች የተመራው የኮሚኒስት አምባገነንነትን የተቃወመውና ጀርመንን በድጋሚ ያዋኸደው ሰላማዊ ሰልፍ፣ እንዲሁም በሱዳን አምባገነኑን ኦማር አልበሽርን የተቃወመዉና በሙያ ማህበራትና በተለያዩ የሴቶች ቡድን የተመራው፣ በሌላ አገሮች የተደረጉት ወጤታማ ህዝባዊ እምቢተኝነት ጥንካሬና ድክመት ማወቅ በመጠኑም ቢሆን ለኢትዮጵያ ሁኔታ ይረዳል።

**፪) የህንዱ ህዝባዊ እምቢተኝነት፥** ማሃትማ ጋንዲ የተመራው የጨዉ ጉዞ (Salt March ወይንም Dandi March) ሃያ አራት ቀናትን የፈጀ ወደ 390 ኪ.ሜ የሚርቅ ጨው ወደሚመረትበት አረብ ባህር ጠረፍ ዳንዲ የተደርገ ጉዞ በእንግሊዞች በጨው ላይ የተጣለ ቀረጥን በመቃወም ነበር። ጨዉ ለሁሉም ሰዉ የሚያስፈልግ መሰርታዊ ነገር በመሆኑ የሁሉንም ሰው ቤት እንደሚነካ ተምሳሌታዊ መነሻ ምልክት ሆኖ ህዝቡን ለማስተባበር አገለገለ እንጂ፣ የዚህ አመጽ አልባ እንቅስቃሴ ላዕላይ ግብ ግን፣ የጨው ማግኘት ጉዳይ አልነበረም። የእምቢተኝነቱ ላዕላይ ግብ ሁሉንም በደረጃ (ካስት) የተከፋፈለ የህንድ ህዝብ አስተባብሮ፣ የእንግሊዝን የቅኝ አገዛዝና ኢፍትሃዊነት ለማስወገድ ነበር። ይህ ሚሊዮኖችን ያንቀሳቀሰ ትግል በህዝባዊ እምቢተኝነት በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ያለውን የምልክትን/ተምሳሌታዊ መነሻን/ አስፈላጊነት ያሳያል።

እንዲሁም ይህ የሞራል ልዕልና የነበረው ህዝባዊ እምቢተኝነት በአጠቃላይ በአገሪቱ ተቀጣጥሎ የህንድን ብሄራው ኮንግረስ ተቀባይነት እንዲኖረውና እምቢተኝነቱ አለማቀፋዊ ተሰሚነት እንዲኖረው ሆኗል። ከዚህ ሕዝባዊ እምቢተኝነት የምንማረው አንዱ ቁም ነገር አመላካች ድርጊት (symbloic act) የአብዛኛውን ህዝብ ኑሮ የሚነካና አብዛኛው ህዝብ የሚጋራው ችግር/ ጭቆና/ስቃይ፣ አብዛኛዉን ህዝብ የሚያነሳሳ፣ አካታች ሆኖ፣ ስር የሰደደዉንና መዋቅራዊና ስርዓታዊ የሆነውን በደልና ኢፍትሃዊነት ለማስወገድ እንደመነሻ

ሆኖ ማገልገል ያለበት መሆኑንና ዋናው ግብ ግን የችግሮቹ ሁሉ ምንጭ የሆነውን ጉዳይ ማስወገድ መሆኑ ነው። ትግሉ ተምሳሌታዊ በሆነው በጨው ጉዳይ ይጀምር እንጂ ስልታዊ ግቡ ግን የችግሩ ሰንኮፉ እንዲነቀልና ከስሩ መዋቅራዊ፣ ህጋዊ፣ ስርዓታዊ እና ተቋማዊ ለውጥ ለማምጣት እንደነበረ ትልቅ ትምህርት ያስተምረናል።

**፫) የአሜሪካው ህዝባዊ እምቢተኝነት፥** እንደ አውሮጳዊያን አቆጣጠር በ1955 እና 56 ዓ.ም፣ በሰሜን አሜሪካ፣ በሮዛ ፓርክስ፣ ማርቲን ሉተር ኪንግ፣ እና የአካባቢ ጥቁር ማህበረሰብ መሪነት የተካሄደው ህዝባዊ እምቢተኝነት ብዙ ነገር ያስተምረናል። አፍሪካ አሜሪካዊያን የመንገመሪን የህዝብ ማመላለሻ አውቶቡስ ሮዛ ፓርክስ መቀመጫዋን ለነጭ ሰው አሳልፋ አልሰጥም በማለቷ ከታሰረች በኋላ የህዝብ ማመላለሻዉን ባለመሳፈር አምጽዋል። ከሮዛ ፓርክስ እስራት በኋላ በመንገመሪ የሚገኘው የጥቁር ማህበረሰብ አውቶቡሶችን ከአንድ አመት በላይ ከለከለ። ጊዚያዊ ችግሩን ለመወጣት መፍትሄ አበጀ። በከፍተኛ ደረጃ የተደራጁ፡ የመኪና መጋራት ስርዓት በመከተል፣ የማህበረሰብ ስብሰባዎች፣ የቤተክርስቲያን ተሳትፎ እንዲቀጥልና ትግሉ እንዲፋፋም አደረገ። ይህም የአዉቶብስ ወንበር አንለቅም በሚል የተነሳው ተምሳሌታዊ/ አመልካች እምቢተኝነት ጉልህ ድሎችን አስከትሏል፤ 1) የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ በአውቶቡስ ላይ ሰዎችን በዘራቸው መለያየት ኢሕገመንግሥታዊ ነው በማለት ውሳኔ አስተላለፏል ፣ 2) ብሄራዊ የዜጎች መብት ንቅናቄን ቀስቅሷል፣ 3) ትግሉ መሪዎችን ማውጣት ቻለ። በአሰባሳቢ ራዕዩና ድንቅ ንግግሩ የሚታወቀው ዶ/ር ማርቲን ሉተር ኪንግን እንደ ብሔራዊ መሪ ወደ ታዋቂነት አመጣ። ትግሉ መሪ ፈጠረ፣ 4) የሰሜን አሜሪካ የሲቪል መብቶች ንቅናቄን በአገር አቀፍ ደረጃ አደራጀ። ይህም የአካባቢ፣ የሰለጠነ፣ ሰላማዊ የጋራ ተቃውሞ ግልጽ ራዕይ ኖሮት በጠንካራ አመራር እና ቅንጅት፣ የዘረኝነት ስርዓትን ኢኮኖሚ ማነቃነቅ ቻለ።

ከዚህ ህዝባዊ እምቢተኝነት ከምንማራቸው ቁም ነገሮች አንዱ የተቀናጀና አካታች፣ ቀጣይነት ያለው፣ ግልጽና አሰባሳቢ ራዕይ ያለው፣ ነዉጥ-አልባ፣ በስነምግባር የተመራ በአንድ አካባቢ የተጀመረ ህዝባዊ እምቢተኝነንት አድጎ የስርዓቱ ኢፍትሃዊነትን ለመፈታተንና ሀገራዊ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል መሆኑን ነው። ነዉጥ አልባ እና በበቀል ላይ ያላተኮረ ህዝባዊ እምቢተኝነት ዘርን አልፎ የብዙ ህዝብን ርህራሄ ሊያስገኝና፣ ጨቋኝ ስርዓቶችን ማግለል እና ዘላቂ ለውጥ ማምጣት ያስችላል። እንዲሁም ህዝብ በሃይማኖት ኢኮኖሚና በዘር ሳይከፋፈል ለፍትህ እንዲቆም አድርጓል። በተከፋፈለ ማህበረሰብ አካታች በሆነና የሞራል የበላይነት ባለው አመራር ኢፍትሃዊነትን በጋራ ለመታገል ረድቷል።

**፬) የደቡብ አፍሪካው ጸረ-አፓርታይድ ትግል፥** ሌላው ህዝባዊ እምቢተኝነት ደግሞ የደቡብ አፍሪካ ፀረ-አፓርታይድ ንቅናቄ ነው። ይህም በሕዝባዊ እምቢተኝነት ተጀምሮ ወደ ብሔራዊ እና ዓለም አቀፍ ማዕቀቦች እና ተቃውሞ ያደገ ነው። በዚህ የአፍሪካ ብሄራዊ ኮንግረስ፣ ኔልሰን ማንዴላ እና ሌሎች አንቂዎች የመሩት ትግል በሺዎች የሚቆጠሩ በጎ ፈቃደኞች የአፓርታይድን ህግጋት ሆን ብለው ጥሰዋል—“ነጭ-ብቻ” አካባቢዎች ገብተው የተለዩ አገልግሎቶችን ተጠቅመዋል። በዚህም የአፓርታይድን ከፋፋይ ህግ ሆን ብለው ጥሰዋል። በዚህም ሰላማዊ ተቃውሞዉ የአፓርታይድን ጭካኔ በማጋለጥ አለም አቀፍ ትብብርን እንዲኖር አድርገዋል። ይህም ለሰፊ የህዝብ ንቅናቄ መሰረት ጥሏል።

እምቢተኝነቱም ህዝቡን ሊያሰባስብ የሚችል ግልጽ ራዕይ ነበረው። “የቀስተ ደመና ሀገር" የሚለዉንና አሰባሳቢ/አካታች የሆነ ራዕይ ይዟል። በቀል ሳይሆን፣ ሁሉን አቀፍ ብሄራዊ ማንነት እና የጋራ ፍትሃዊነት ላይ ያተኮረ ራዕይ አንግቧል። አፓርታይድን እንደ ስርዓት አብዛኛዉን ህዝብ የሚጎዳ መሆኑን በግልጽ አሳይቷል። የትግሉ መሪዎችም የሞራል የበላይነትና ጽናትን አሳይተዋል። ፍትሃዊ ያልሆኑ ህጎች ላይ

ያነጣጠረው ህዝባዊ እምቢተኝነት የስርዓቱ ጭካኔን ለአለም በማጋለጥ ትግሉን አለማቀፋዊ በማድረግ ከአለም አቀፍ ማህበረሰቡ ድጋፍ ማግኘት ተችሏል። በዚህ መልክ የተጀመረው የጸረ-አፓርታይድ እንቅስቃሴ ውሎ አድሮ የስርዓት ለውጥ እንዲመጣ አድርጓል። እንዲሁም አካታች የሽግግር ስርዓት መስርቷል። ከአፓርታይድ በተደረገው ሽግግር ወቅት የዴሞክራቲክ ደቡብ አፍሪካ ኮንቬንሽን ዋና ዋና የፖለቲካ ፓርቲዎችን (ኤኤንሲ፣ ብሄራዊ ፓርቲ) ብቻ ሳይሆን የሰራተኛ ማህበራት፣ የንግድ ማህበራት የባህል መሪዎችን፣ የሃይማኖት ድርጅቶችን እና የሲቪል ማህበረሰብን ያካተተ ነበር። ሁሉንም የተጎዱ ባላድርሻዎች ማካተቱ ለድርድር ሂደት ህጋዊነትን ለመገንባት ረድቷል።

**፩) የሱዳንና ግብጽ ህዝባዊ እምቢተኝነቶች፥** በቅርብ ጊዜ ሱዳንና በግብጽ የተደረጉት ህዝባዊ እምቢተኝነቶችም የሚያስተምሩን ነገር አለ። ሁለቱም አምባገነን መሪዎችን ከስልጣን ማዉረድ ችለዋል። ሆኖም ግን መጨረሻቸው አላማረም። በሱዳን እና በግብፅ የተቀሰቀሰው ህዝባዊ እምቢተኝነት የነፃነት እና የፍትህ ጥያቄዎችን ያቀፈ ቢሆንም በውስጥ እና በውጫዊ ሁኔታዎች ወደ ዴሞክራሲ መሸጋገር አልቻሉም። በ 2019 እ. ኤ. አ. በሱዳን ንቁ ማህበራት፣ እንደ ባለሙያዎች ማህበር፣ የሴቶች ቡድኖች፣ እና ወጣቶች ማህበር የሚመራ ከፍተኛ የተቃውሞ እንቅስቃሴ በሚያስድምም ሁኔታ ተከስቷል። ዋና ተልዕኮውም ህዝቡን እየጎዳ ያለዉን ወታደር አልተባበርም በማለት፣ ለ30 አመታት የቆየውን አምባገነኑን ኦማር አልበሽርን አስወገደ ። ከዚያም በወታደሩ እና በሲቪሎች መካከል የስልጣን መጋራት ስምምነት ተደረጎ ወታደራዊ - ሲቪል ጥምር የሽግግር መንግስት (ወታደራዊ-ሲቪል ጥምር የሽግግር ምክር ቤት) ተቋቁመ። ነገር ግን ብዙ የአገሪቱን ሃብት እንደ ወርቅ፣ ባንኮች፣ ኢንዱስትሪዎች ያሉትን ተቆጣጥሮ የቆየውና በውጭ ሃይሎች ቁጥጥር ስር የወደቀው ብሄራው የጦር ሰራዊት አመራር ስልጣኑን ሙሉ በሙሉ አሳልፎ መስጠት አልፈለገም።

የሲቪል መሪዎች እና የተቃውሞ እንቅስቃሴዎችን የመሩት (ለምሳሌ SPA፣ የነፃነትና የለውጥ ኃይሎች) ጠንካራ ቅንጅት አልነበራቸውም። በመሆኑም በድርድር ስልቶች እና በፖለቲካዊ የስልጣን ክፍፍል ላይ ጠንክረው መዉጣትና አወንታዊ ተጽዕኖ መፍጠር አልቻሉም። የሽግግር መንግስቱ በሰላማዊ ሰልፈኞች ላይ ለሚደርሰው ግድያ፣ እንዲሁም ለተከተለው የኢኮኖሚ ችግር መፍትሄ በፍጥነት መስጠትም አልቻለም። ይህም ህዝባዊ ብስጭት ፈጠረ እና ለዴሞክራሲያዊ መሪዎች ህዝቡ የሚሰጠውን ድጋፍ ቀነሰው። በተጨማሪም የቀጠናው ኃያላን (አረብ ኤመሬትስ፣ ግብፅ፣ ሳውዲአረቢያ፣ ሩሲያ) ገንዘብ፣ ጦር መሳሪያ እና የፖለቲካ ድጋፍ ለወታደራዊ መሪዎቹ ሰጡ። ጥቅምት 2021 ፡ ወታደራዊ መፈንቅለ መንግስት በጄኔራል ቡርሃን እና በጄኔራል ሄሜቲ (አር ኤስ ኤፍ) ተካሄደ። በመፈንቅለ መንግስቱ የሲቪሉን መንግስት በትኖ ሙሉ ቁጥጥር ወደ ወታደራዊ አገዛዝ ተመለሰ። ቀደም ብሎም ቢሆን ወታደራዊ እና የስለላ አገልግሎቶችን የኢኮኖሚ ተቋማትን፣ ደህንነትን እና ቁልፍ የመንግስት ተቋማት ላይ ወታደሩ በቁጥጥር ስር አድርጎ ነበር።

ሱዳን ለረጅም ጊዜ የቆዩ የውስጥ ግጭቶች ለምሳሌ እንደ ዳርፉር ነበሩ። ወታደሩም ለሰላም ብችኛ አለኝታ አድርጎ ራሱን አቀረበ። በዚህም በወታደራዊ አንጃዎች ተጠቅመው ዲሞክራሲያዊ ለውጦችን ለማዘግየት ሰሩ። ከሚያዚያ 2023 እስከአሁን አሁን ያለው በወታደራዊ አመራሩ እና በRSF መካከል የእርስ በርስ ጦርነት ተቀሰቀሰ። ከዚህ የምንማረው የሲቪሉ ህዝባዊ እምቢተኝነት ለጊዜው አምባገነኑን ለማዉረድ ቢረዳም፣ በአግባቡ ጠንካራ ድርጅት ባለመመስረቱ እና፣ የተቀናጀ ጠንካራ የሲቪል አመራር ባለመኖሩ፣

የዉጭ ሃይሎች ተጨምረዉበት ስልጣን በወታደሩ እንዲነጠቅ፣ መልሶም ወታደራዊ አገዛዝ እንዲሰፍን እና ብጥብጥ እንዲቀጥል ሆኗል።

በ2011 እ.ኤ.አ በግብጽ በሆስኒ ሙባረክ ላይ የተቀሰቀሰው ተቃውሞ "ዳቦ፣ ነፃነት እና ማህበራዊ ፍትህን" ጠይቋል፣ ብዙዎችን አንቀሳቅሷል። በዚህም የከተማ ወጣቶች እና ዓለማዊ /secular/ ቡድኖች ተሳትፈዋል። ሙባረክ ከስልጣን ወረዱ፤ ወታደሮቹ ስልጣኑን በጦር ኃይሎች ጠቅላይ ምክር ቤት (SCAF) ሥር ተቆጣጠሩ ። ከ2012-2013 ግብፅ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ አካሄደች የሙስሊም ወንድማማችነቱ መሐመድ ሙርሲ ፕሬዚዳንት ሆኑ። ነገር ግን በእስልምና አክራሪዎችና እና በዓለማዊ ኃይሎች እንዲሁም በወታደር ደጋፊዎች መካከል ልዩነቱ ሰፍቶና ጥልቅ መከፋፈል ተፈጥሮ ጽንፍ ያዙ። ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ለማስፈን ምርጫ ብቻ ሳይሆን ጠንካራና ገለልተኛ ተቋማት ሊገነቡ ይገባ ነበር።

ግብጽ የሲቪል ማህበረሰብ የሚደግፉ ነፃ የዴሞክራሲ ተቋማት አልነበሯትም። ወታደራዊ ክፍሉ በኢኮኖሚው ከሁለት ሶስተኛ ድርሻን ለብዙ አስርት አመታት ስለተቆጣጠረ በዚህም ግብጽ ሚሊታሪያዊ ህብረተሰብ እየተባለች ትጠራለች። በዚህም ጉድለት የሲቪል ማህበርሰቡ ብዙ ተጽዕኖ መፍጠር አልቻለም። በመጨረሻም በጦሩ አዛዡ በጀኔራል አብደል ፋታህ ኤል-ሲሲ የሚመራው ወታደራዊ ኃይል መፈንቅለ መንግስት በማድረግ ስልጣኑን ተቆጣጠረ። ወታደሩ በግብፅ የፍትህ፣ የፕሬስ፣ ወታደሮቹ ትርምስንና ሽብርተኝነትን መከላከል የምንችል እኛ ብቻነን ብለው ራሳቸውን ብቸኛ አማራጭ አድርገው አቀረቡ። ከ2013 በኋላ፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ሚዲያዎች፣ አክቲቪስቶች እና ተቃዋሚ ፓርቲዎች ላይ ጭካኔ የተሞላበት እርምጃ ተወሰደ። በሳውዲ አረቢያ እና የተባበሩት አረብ ኤምሬትስ ያሉ የባህረ ሰላጤው ሀገራት የፖለቲካ እስልምና እንዳይነሳ ሲሲን ደገፉ። በግብጽ የወታደራዊ ጣልቃገብነት፣ የተከፋፈለ የሲቪል አመራር፣ ደካማ ተቋማት፣ የህዝብ አለመረጋጋት ስጋት፣ የኢኮኖሚ ችግር፣ እና ውጫዊ ተጽዕኖ ተጨምሮበት፡ የህዝባዊ እምቢተኝነቱ ጨነገፈ። በዚህም ስልጣን በወታደሩ ስር ገባ።

ከግብጽና ሱዳን ልምዶች የምንማረው ህዝባዊ እምቢተኝነት ዉጤታማ እንዲሆን የተደራጁ ተቋማት፣ ያስፈልጉታል። የዲሞክራሲ ባህል እና ልምምድ እጥረት በአለበትና ወታደሩ የአገሪቱን ስልጣንና ሃብት በተቆጣጠረበት አገሮች ስልጣን በወታደሩ እንዳይነጠቅ ልዩ ጥንቃቄ ያስፈልጋል። እንዲሁም የወታደሩን ጣልቃ ገብነት መገደብና ስልጣን እንዳይነጥቅ ነቅቶ መጠበቅ፣ በሲቪል ድርጅቶ መካከል ቅንጅት መፍጠር፣ የጂኦፖለቲካ ጉዳዮች ማስተዋልና ለዚያ ምላሽ የሚሰጥ ስልት መንደፍ፣ እና ምርጫ ብቻ ሳይሆን ዲሞክራሲያዊ ተቋማትን መገንባትና መብቶችን በተግባር ማስከበር ይገባል። ለዉጡ እንዲረጋና ህዝቡ እንዳይማረር የኢኮኖሚ አለመረጋጋትን ወይም ቀዉስን በአስቸኳይ ለመፍታት ሳይዘገዩ ጥረት ማድረግም ያስፈልጋል።

በተጨማሪም የሕንድና የደቡብ አፍሪካ ትግሎች ከፀረ-ቅኝ ገዥነት ከሰፋሪ ገዥነት ጋር ስለተያያዙ ሕዝቡን ለማስተባበር የተደረገውን ጥረት ቀላል ማድረጉን መገንዘብ ግድ ይላል። እንዲሁም በአሜሪካ ለነጮች ብቻ የነበረ ነገር ግን የህግ የበላይነትን ያከበረ የህገመንግስታዊ ስርዓት መኖሩ የተገለሉ ሁሉ የዜግነት ህገመንግስታዊ መብቶቻችን ይከበሩልን ሲሉ በመጨረሻ ሰፊ ድጋፍ ከአጋሮች አግኝተው ስኬታማ ሆነዋል። ኢትዮጵያ ግን ዲሞክራሲያዊ ህገመንግስትና የህግ የበላይነት የሌሉባት አገር ስለሆነችና በአሁኑ ጊዜ በማያባራ የርስበርስ ጦርነት ስለወደቀች አብዛኛዎቹ ከውጭ የሚኮረጁ የትግል ስልቶች ፍሬያማ የሚሆኑ አይመስሉም። ስለዚህ በአገራችን የፖለቲካ አውድ ያገኘናቸውን ጠቃሚ ትምህርቶች ጨምቀን ማውጣት ግድ ይላል።

## ሐ. ካለፉት የኢትዮጵያ ህዝባዊ እምቢተኝነቶች ምን እንማራለን

በአጼ ኃይለስላሴ ዘመነ መንግስት ጀምሮ ኤርትራ እስከምትገነጠል ድረስ በሃገር ዉስጥና በዉጭ በነበሩ ተማሪዎችና በተማሩ ዜጎች የሚመራና የንጉሱን የጭቆና አገዛዝ ለመጣል ያለመ ህዝባዊ እምቢተኝነት እንቅስቃሴ ተደርጓል። ትግሉ አገር በቀል ራዕይ የሌለዉ በመሆኑ ወደ ምስራቁ ርዕዮተአለም አመዝኗል። ምንም እንኳ አንድ አንድ ወጣቶች በተውሰነ ነገድ በይበልጥም በአማራው ላይ ህዝብን የሚያነሳሳ የጥላቻ ቅስቀሳ ቢያደርጉም፣ አብዛኛው ወጣቶች በነገድ ሆነ በመደብ ሳይከፋፈሉ ለአገር በጎ ምኞት ኖሯዋቸው ያደርጉት ትግል ነበር። ወጣቶቹም በሞራል ልዕልና ኖሯቸው ለተጎዳው ህዝብ ቆመዋል፣ መስዋዕትነትም ከፍለዋል።

የተማሪዎቹ እንቅስቅቃሴ ተስፋፍቶ በሰራተኛ ማህበር፣ በመምህራን፣ በታክሲ ነጂዎችና በወታደሩ ዉስጥ እንዲፈጠር አድርገዋል። ነገር ግን ክፍተቱን ያየው ወታደራዊ ደርግ ንጉሱን ከስልጣን አዉርዶ ስልጣኑን በአቋራጭ ተቆጣጠረው። እምቢተኝነቱ ወደኋላ ላይ በአይዲዮሎጂ ተከፋፍሎ ኢህአፓ፣ መኢሶን እና በሌሎችም ድርጅቶች ተከፋፍሎ፣ በበጎ ራዕይ ትግሉን የጀመሩት ለዉጥ ፈላጊ ወጣቶች እርስ በርሳቸው ተገዳደሉ። በይበልጥ የደርግን ጨካኝ የቀይ ሽብር እርምጃ ተከትሎ በፖለቲካው ስልጣን ላይ ቆይተው የረባ ተጽዕኖ መፍጠር አልቻሉም። እንዲሁም በምስራቁ አይዲዮሎጂ ላይ መጣበቃቸው የአገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ፣ ባህልና እና የአገር ግንባታ ታሪክን ብዙም ከግምት ዉስጥ አላስገቡም ነበር። በዚያን ጊዜ የጀመረው አንድ አንድ ክፍፍልና በአማራ ላይ በራሱ ልጆች ጭምር በተደረገው የተሳሳተ መልዕክት ቀስ በቀስ ወደ ቋንቋን/ነገድን መሰረት ያደረገ የዘውግ ፖለቲካ ተቀይሮ አማራን እንደ ገዢ መደብ በመቁጠር በአማራው ላይ በተደረገው የጥላቻ ዘመቻ አሁን ድረስ አማራ ዘሩ እየተቆጠረ ዘር ማጥፋት እየተፈጸመበት ነው። የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንንም ማሳደድ የመጣው ሃሳብ ከዚያ የመጣ ነው። ኢትዮጵያም አሁን አበሳዋን እያየች ነው።

ደርግ በወሰደዉ ጨካኝ እርምጃ ካመከነው በኋላ አልፎ አልፎ የነበረው የተማሪዎች እንቅስቃሴ ሶስት ዋና ዋና ድክመቶች ነበሩት፤ 1) ተማሪዎች ድርጅትና መሪ አልነበራቸውም፣ 2) የተማሪዎችን ጥያቄና ግብ የሚያሳይ ፍኖተ ካርታ አልነበረም፣ 3) አገር በቀል ራዕይ አልነበራቸው። የሙያ ማህበራት /የሲቪል ማህበራት/ እንቅስቃሴውም እንደዚሁ የሚከተሉት ድክመቶች ነበሩበት፤ 1) የፖለቲካ ተሳትፎና ልምድ ያላቸው የሙያ ማህበራት መሪዎች አልነበሩትም፣ 2) የሙያ ማህበሩ፣ አሁንም እንደሚደረገው፣ በመንግስት ይጠለፋሉ። ለሰራተኛው መብት እና ለሙያቸው በመቆም ፋንታ የመንግስትን ተልዕኮ አስፈጻሚ ይሆናሉ፣ 3) በመብት መከበርና በመሳሰሉ መስክ የተሰማሩ አትራፊ ያልሆኑና የመንግስት ያልሆኑ ድርጅቶች መንግስት በአፋኝ ህጉ ስለሚያስፈራራቸው ስለሚያሳድዳቸዉ እና ስለሚጠልፋቸው፣ ህዝቡን ለመብቱ እንዲነሳ ማስተማር አልቻሉም። በዚህም የኢትዮጵያ ህዝብ ከገዢዎቹ አፈና እንዳይወጣ ሆኗል።

አፋኝ በነበረው የደርግ ጊዜ፣ ከቀይ ሽብር በኋላ፣ አልፎ አልፎ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ያደርጉት ከነበረው ድምጽ ማሰማት ዉጭ፣ የተደራጀ ህዝባዊ እምቢተኝነት በከተማ ዉስጥ ማድረግ የሚታሰብ አልነበረም። በከተማ አካባቢ የነበረው የፖለቲካ ፓርቲዎች እንቅስቃሴ የተወሰነው ህቡዕ ሆኖ ሲቀጥል ሌላው ወደ ለየለት ትጥቅ ትግል ገባ። በዚህም አንድ አንዶቹ አገራዊ ራዕይ ያላቸው ሲሆን እንደ ህወሃት፣ ኦነግ፣ ኦብነግና ሻቢያ የመሳሳሉት የመገንጠል ወይንም ወጣንበት የሚሉትን ነገድ ጥቅም ለማስከበር ያለሙ

ነበር። እነዚህንም ድርጅቶች በደርግ አገዛዝና በተራዘመው ጦርነት የተማረረውን ህዝብ ማነሳሳትና ድጋፍ ማግኘት ችለዋል። የምስራቁ አለም አይዲዮሎጂ መዳከሙም ደርግን ድጋፍ እንዲያጣ አደረገው። በይበልጥ ህወሃትና ሻቢያ ባደረጉት የተቀናጀ ጦርነትና በምዕራባዊያንና በአረቦች በተደረገላቸው እርዳታ፣ የተሰላቸውን የደርግ መንግስት ጦር አሸንፈው ብዙዉንም ህዝብ አታለው ስልጣኑን ያዙ። ኤርትራንም ገነጠሉ። ኢትዮጵያንም የባህር በር አሳጥተው በነገድ አስተዳደር ከፋፈሏት።

በህወሃት የሚመራው የኢህአዲግ አገዛዝ መጀመሪያ አካባቢ ዲሞክራሲያው እና ለህዝብ አሳቢ ቢመስልም ብዙ ሳይቆይ በህዝብ ላይ ጨካኝ እርምጃ መዉሰድ ጀመረ። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን ጨምሮ በአንዳንድ ከፍተኛ ትምህርት ቤቶች አንዳንድ የህዝባዊ እምቢተኝነት ሙከራዎች የነበሩ ቢሆንም በዕለታዊ ጉዳይ ላይ ያተኮሩ፣ ያልተቀናጁና ቦግ እልም የሚሉ ነበሩ። መንግስት ከጊዜ ወደጊዜ የነገድ  ክፍፍል ፖለቲካዉን በወጣቱ ዘንድ እያሰረጸ ሲሄድ ተማሪዉን፣ ህዝቡንና ተቋማቱን በነገድ ሲከፋፍል የተቀናጀ የተማሪዎች እንቅስቃሴ ማድረግ አስቸጋሪ ሆነ።

በፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ መሪነት በመአህድ ተጀመሮ የነበረው አማራን ከጭፍጨፋ የማዳን እንቅስቃሴ አብዛኛው አማራው ራሱ እየመጣበት ያለውን አደጋ በበቂ ሁኔታ ባለመገንዘቡና ራሱን ለማዳን ባለመንቃቱና ባለመደራጀቱ የህወሃት ጨካኝ እርምጃ ተጨምሮበት ሳይቀጥል ቀርቷል። በምርጫ 97 በቅንጅት ፖለቲካ የተደረገው ተስፋ ሰጭ የህዝብ እንቅስቃሴ በወያኔ አፈናና የቅንጂት መሪዎች መከፋፈል ተጨምሮበት መከነ።

በኢህአዲግ የመጨረሻዎቹ አመታት ግን፣ በይበልጥ በአማራና በኦሮሚያ፣ የህወሃትን የበላይነት፣ አድሎ፣ የመሬት ነጠቃ፣ ሰብዓዊ መብት ረገጣና ግድያ በመቃወም ጠንካራ ህዝባዊ እምቢተኝነት ተቀሰቀሰ። ለዚህም የማህበራዊ ሚዲያ ቅስቀሳ ትልቅ ሚና ተጫውቷል። እንዲሁም በአማራና ኦሮሚያ ክልል መካከል የነበረዉን ትግል ለማቀናጀት የተደረገው ሙከራ፣ ለምሳሌ በጎንደር በተካሄደው ሰልፍ  "የኦሮሞ ደም ደሜ ነው" የሚለው አባባል፣ ትልቅ የቅንጅት መልዕክት ማስተላለፍና መንግስትን ማርበትበት ችሏል። እንዲሁም በባህርዳር፣ ጎንደርና፣ ኦሮሚያ ወዘተ ደረታቸውን በጀግንነት ለጥይት ሰጥተው ድምጻቸውን ያሰሙ ወጣቶች አስተዋጾ ግዙፍ ነበር። ነገር ግን ትግሉ ግልጽ የሆነ አገራዊ ራዕይ እና አገራዊ አደረጃጀት ስላልነበረው፣ አሁንም  በሚያሳዝን ሁኔታ፣ አፈጮሌዎችና ድብቅ አጀንዳ ያነገበው አቢይ አህመድና ሌሎች የኢሃዲግ ባለስልጣናት አጋጣሚዉን ተጠቅሞ ስልጣኑን ተቆጣጠሩ። ኢትዮጵያዊ ራዕይ አለን ያሉትም እንደ ግንቦት ሰባት ያሉ ድርጅቶችና መሪዎቻቸው እንዲሁም ለአማራ መብት እንቆማለን ያሉት እነ አብን ህዝቡን ሜዳ ላይ ጥለውትና በስልጣን ተገዝተውና ከድተው በገዢው መንግስት ስር ተለጠፉ። ህዝቡን በፖለቲካ መሪዎች ላይ ተስፋ እንዲቆርጥና እንዳይተማመን አደርጉት።  ከዚያም የኦሮሞ ኦህዲድ በብቸኛነት ፈላጭ ቆራጭ ሆኖ የኦነግን አላማ በከፋ ሁኔታ ማስፈጸም ቀጠለ። በአማራው ላይ የሚደረገው ዘር ማጥፋት ተባብሶ ቀጠለ። ኢትዮጵያም ከድጡ ወደ ማጡ ገባች።

ከታሪካችን ተምረን፣ የጠራና ዉጤታማ ህዝባዊ እምቢተኝነት ማካሄድ፣ መንግስትን ከስልጣን ከማዉረድ ባለፈ ስለምንተካው አዲስ መንግስትና የአስተዳደር ስርዓት ግልጽ ራዕይ፣ እቅድና ፍኖተ-ካርታ ሊኖረን ይገባል። ከንጉሱ ጊዜ ጀምሮ ባየነው፣ ፕሮፕፌሰር መስፍን ወልደማሪያም እንዳሉት፣ የኢትዮጵያ ህዝብ እምቢተኝነት ከስልጣን መንቀል እንጂ መትከል አልቻለም። ተገቢዉንና ለአገር የሚበጀውን ስልጣን ላይ አላወጣም። ለአገር የሚጠቅም ስርዓት፣ መዋቅርና ተቋም አልዘረጋም።  አሁንም የሚደረገው ህዝባዊ እምቢተኝነት፣ የአገሪቱን ስልጣን ለመሞጭለፍ በአማራ ጥላቻ በነገድ ተደራጅተው አስፍስፈው ለሚጠብቁ

ወይንም ወታደራዊ ሃይሉን ለተቆጣጠሩት አምባገነኖችና ዘረኞች አሳልፎ እንዳይሰጥ ልዩ ጥንቃቄ ያስፈልገዋል።

ትግሉ ግልጽ አገራዊ ራዕይና ፍኖተ-ካርታ፣ በአግባቡ የተደራጀና ተጠያቂነትን የሚቀበል አመራር ሊኖረው ይገባል። ህዝቡም ትግሉ አሳታፊ እንዲሆንና መስመሩን እንዳይለቅ ምንጊዜም ንቁ ተሳትፎና ቁጥጥር ማድረግ አለበት። የግለሰቦችን አምባገነናዊነት ከጅምሩ መቃወም ይገባል። ኢትዮጵያን ግልጽ በሆነ ራዕይና ፍኖተ ካርታ መርቶ ወደ ዲሞክራሲና የህግ የበላይነት ለማሸጋገር ሁሉም ኢትዮጵያዊ እኩል ሃላፊነት ሊኖረው ይገባል። የአገራችን ጉዳይ በግልጽ በመርህ የሚመራ እንጂ በተወሰኑ ግለሰቦች ፍላጎትና ምኞት የሚወሰን መሆን የለበትም። ለዚህም ጠንካራ ድርጅት ያስፈልጋል። ለህዝባዊ እምቢተኝነቱ ሁሉም አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ አስተዋጾ ሊያደርግ ይገባል።

# መ. ምክረ ሃሳቦች ለሰላማዊ ንቅናቄ

የወቅቱ የኢትዮጵያ የሕዝባዊ እምቢተኝነት ስትራቴጂ የሚከተሉት በሁለገብነት የተሳሰሩ መርሆች፣ ግንዛቤዎች፣ አላማዎችና ግቦች በጥራት እንዲቀመጡ ጥረት ማድረግ ይጠበቅበታል።

**መሰረታዊ ግንዛቤዎች**

1. **በነገድ መካከል ልዩነትን ማጥበብና የዜጎችና የአገሪቱ በሽታ የሆነውን አገዛዝና ነገድ ከፋፋይ ስርዓት መጣል ላይ ማትኮር፦** ለአመታት በህዝቡ መካከል የተረጨ መርዘኛና ከፋፋይ የጥላቻ ቅስቀሳዎችና ወጣቱ ትውልድ ከአንድነትና ከአገር ፍቅር ይልቅ የዘውግ ክፍፍልን እየተሰበከ ከፋፋይ በሆነ ስርዓተትምህርት አልፏል። በዚህም የተነሳ በምክንያታዊነት ማሰብ እንዳይችል ተደርጎ ያደገ መሆኑን በመገንዘብ፣ የተፈጠረውን መከፋፈል መረዳትና፣ መንግስት በአብዛኛው ህዝብ ላይ እያደረሰ ያለዉን በደል ለይቶ ማወቅ ተገቢ ነው። ለምሳሌ በአገዛዙ ጦር በግፍ መጨፍጨፍ፣ ህዝብን እርስ በርሱ ማዋጋት፣ መፈናቀል፣ መታፈን መሰወር፣ እና መገደል፣ በግድ አፍሶ ወደ ወታደራዊ ስልጠና መላክ፣ አስገደዶ ወደ ጦርነት መማገድ፣ ጭቆና፣ የፖለቲካ ነፃነት እጦት፣ የኢኮኖሚ ኢፍትሃዊነት፣ አድልዎ፣ የግብር መጨመር፣ ከስራ ማባረር፣ በነጻነት ተንቀሳቅሶ መስራት አለመቻል፣ በሃይማኖት ተቋማት ላይ የሚደረግ ጥቃት፣ ወዘተ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ የሚጋራቸው ችግሮች ናቸው።

   በተጨማሪም የኢኮኖሚ ፖሊሲው አንድን ነገድ ለመጥቀም መቀየሱ፣ ሙስና ታይቶ በማይታወቅ መጠን መንሠራፋቱ፣ ሕዝብ ዳቦ ሲል ጥይት እናመርትልሀለን መባሉ፣ አጠቃላይ ሕዝቡ ተስፋው መጨለሙ፣ የዓለም አቀፍ የልማት ተቋማት (አይ ኤም ኤፍ) ለአገርና ሕዝብ መሻሻል ሳይሆን በተቃራኒው ሕዝብ የሚረገጥበት፣ የሚጎሳቆልበትና የሚገፋበት ፖሊስን መደገፍ፣ ወዘተ። በዚህም ትግሉ ሁሉንም ዜጋ ባካተተ መልኩ ከጫፍ እስከጫፍ ለፍትህ እና ለነጻነት የሚደረግ የጋራ ግብ ያለው መሆኑን ማጉላት። አገዛዙ ስልጣኑን ለማራዘም ሃብት ለመመዝበር ህዝቡን በነገድ በመከፋፈል እርስ በርስ በማጣላት፣ በገንዘብ በመደለል የተቃዋሚውን ክፍሎች ለማዳከም ሊሞክር እንደሚችል ቀድሞ ማወቅና

ለመፍትሄዉም ቀድሞ መዘጋጀት ይገባል። ይህንን ለመከላከል በአላማ እና በራዕይ አንድ በመሆን በጥሩ ስነብግባር መስራትና ትብብር መፍጠር ይገባል።

2. **በነገዶች፣ በሃይማኖቶችና በአካባቢዎች መካከል ትብብር መፍጠር፡-** የኢትዮጵያን የግዛት አንድነትና ኢትዮጵያዊነትን ከሚቀበሉ ከሁሉም ማህበረሰቦች ከተውጣጡ መሪዎች፣ ሲቪልና የሙያ ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ የሃይማኖት መሪዎች እና አንቂዎች ጋዜጠኞች ጋር ትብብር መፍጠር ያስፈልጋል። በዚህም አብዛኛዉን ኢትዮጵያዊ በንቅናቄው ውስጥ ማካተት እና እውቀቱንም ሆነ መዋዕለ ነዋዩን በመጠቀም ወደ ጋራው ላዕላይ ግብ መድረስ ይቻላል። ችግሩ የአብዛኛዉን ዜጋ ህይወት የሚያውክ መሆኑንና ችግሩን ስቃዩን የሚጋሩ መሆኑን በመገንዘብ፣ በነገዶች መካካል ቅንጅትና ትብብር መፍጠር ግድ ይሆናል። በአሁኑ ወቅት ብዙ የአማራው ሕዝብ የሚኖረው በሌሎች ክልሎች ነው። የአማራውን ያህል ባይሆንም ሌሎች ዜጎች ለምሳሌ ጉራጌ፣ ወላይታ፣ አፋር፣ ወዘተ እየተገፉ፣ እየተጨቆኑ ነው። ሕዝቡ ከጠባብና ራስን ከሚያጠፋ ከፋፋይ አስተሳሰብ ወጥቶ፣ ራሱን ከድህነት፣ ጉስቁልና እና ጭቆና ነጻ እንዲያወጣ አገር አቀፍ ጥሪ ለህዝቡ ማቅረብ ያስፈልጋል።

3. **ትግሉ እንዳይጠለፍ ነቅቶ መጠበቅ፡-** በተወሰነ ነገድ የበላይነት የሚመራው መከላከያው እና ጥቂት በነገድ ላይ የተደራጁ ሊሂቃን፣ የሚፈጠረውን ክፍተትና አጋጣሚ ተጠቅመው፣ የህዝቡን ጥያቄ ወደጎን ትተው፣ ስልጣን እንዳይነጥቁ፣ ወይንም እንዳይደራደሩ፣ ወይንም ሌላ ዘረኛ ወደስልጣን አምጥተው በህዝብ ዘንድ የከፋ የነገድ መለያየት እንዳይፈጥሩ መጠንቀቅና፣ ችግሩ ቢከሰት ብሎ ቀደም ብሎ መፍትሄ ማስቀመጥ ይገባል። ቢቻል ከታች ያለውን የአስተዳደር፣ የመከላከያና የጸጥታ የፖሊስ አባላት በትግሉ ዉጤት ተጠቃሚ እንደሚሆኑና ለትግሉ አጋዥ እንዲሆኑ በተከታታይ አስተምሮ ትግሉን እንዲደግፉ ማሳመን ያስፈልጋል።

4. **አመቺ ጊዜና ቦታ መመረጥ፡-** የሕዝባዊ እምቢተኝነት እንቅስቃሴውን ተግባራት ትኩረት በሚሹ ቀናትና ቦታዎች ማድረግ፡- ህዝቡን ለማንቀሳቀስ አመታዊ በዓላትን፣ ብሄራዊ በዓላትን፣ አንዳንድ የህዝቡን በደል የሚያሳዩ ሪፖርቶችን (ለምሳሌ የኑሮ ውድነት ሪፖርት፣ አቢይ አህመድ የአማራንና የትግራይን ህዝብ ለማጥፋት የሰራው ሴራ፣ ወዘተ) ተከትሎ፣ ተቃዉሞ መቀስቀስ ህዝብ ያሰባስባል። ታሪካዊና ታዋቂ ቦታዎችንም መጠቀም ይመከራል። ህዝባዊ ስብሰባዎችን ብዙ ህዝብ በሚሰበሰብበት ቁልፍ ቦታዎች (ለምሳሌ የአለማቀፋዊ ስብሰባወችን፣ መንግስት ህንጻዎች፣ ብሄራዊ ሀውልቶች፣ የህዝብ አደባባዮች) ለትግሉ እንቅሳቃሴ የሚሆን አመቺ ቦታንና ጊዜን መምረጥ ተገቢ ይሆናል፣ ለምሳሌ በመስራቅ ጀርመን የሶቪያት ህብረትን መበተንን ተከትሎ እንደተደረገው አይነት እንቅቃሴ፣

5. **አስቸኳይ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች፡-** በህዝባዊ እምቢተኝነቱ ጊዜም ሆነ ያንን ተከትሎ በሚመጣ ለውጥ ህዝቡ እንዳይማረርና ለትግሉ ድጋፉን እንዳያቋርጥ የኢኮኖሚና የሰላም እጦች፣ የአግልግሎት መስጫ ችግሮችን በአስቸኳይ ለመፍታት ስልት ማዘጋጀትና ህዝቡን የሚያሳትፍ ተስፋ ሰጪ ስራ በትምህርት፣ በጤና አገልግሎት በመብራት፣ በዉሃ፣ በትራንስፖርት በመሳሰሉት መስራት፣ የግድ ያስፈልጋል። ለዚህም ጊዚያዊ መፍሄ ቀድሞ ማዛጋጀት ተገቢ ነው።

**የአመራርና መዋቅራዊ ጥያቄዎች፡-**

1. **በህዝብ ዘንድ ተቀባይነትና ከበሬታ ያተረፉ መሪዎች አስፈላጊነት፡-** ቢቻል ወገንተኛ የፖለቲካ ድርጅት መሪዎች ሳይሆኑ በህዝብ ዘንድ ተቀባይነትና ከበሪታ ባላቸው፣ የተበላሸ የኋላ ታሪክ የሌላቸው፣ ህዝቡን ነገድንና አካባቢን ተሻግረው ሊያሰባስቡ በሚችሉ፣ ተናግረው የሚያሳምኑ በሲቪል፣ የሙያ፣ የምሁራን ወይንም በምስራቅ ጀርመን እንደታየው በእምነት ተቋማትመሪዎች ቅንጅት የተቋቋመ ጠንካራ የህዝባዊ እምቢተኛነት አመራር ያስፈልጋል። በህዋስ ደረጃ ያልተማከለ አደረጃጀት መፍጠር ያስፈልጋል። በቀላሉ ሊታወቅ የማይችል መዋቅር ያስፍልጋል። ያልተማከለ፣ ተዋረዳዊ ያልሆኑ አንቂዎች እና አደራጆች በየአካባቢያቸው ማህበረሰብ ውስጥ ራሳቸውን ችለው የሚንቀሳቀሱ አውታረ መረቦችን መፍጠር ያስፈልጋል። ይህ አገዛዙ ጥቂት ቁልፍ መሪዎችን ኢላማ ከማድረግና የሕዝባዊ እምቢተኝነቱን ሰርጎ ከመግባትና መዋቅሩን ከማፍረስ ለመከላከል ይረዳል።

2. **የሕዝባዊ እምቢተኝነቱ አመራር ግልጽነት እና ተጠያቂነት፡-** መሪዎች ለህዝቡ ቀጥተኛ ምላሽ የሚሰጡበት ግልጽ እና ተጠያቂነት ያለው እንቅስቃሴ በማካሄድ የትኛውም ነገድ የመገለል ስሜት እንዳይሰማው ማድረግ ይገባቸዋል።

   **የሕዝባዊ እምቢተኝነቱ አመራር ከተገፉና ለህልዉና ከሚታገሉ ድርጅቶች ጋር በቅርብ በመናበብ መስራት፡-**ይሕ አሰራር ዘላቂና ጠንካራ የጀርባ አጥንትን ያፈጥራል፤ የፖለቲካና የታጠቁ ድርጅቶች ወደ አግላይነት እንዳያዘምሙም ልጓም ይፍጥራል። ትግሉም ለስልጣን በቀረቡ ሌላ የወደፊት አምባገነኖች እንዳይጠለፍና ህዝቡ ድጋሜ ለስቃይ እንዳይዳረግ ይረዳል።

**የሕዝባዊ እምቢተኝነቱ ምልክትና መሪ መፈክር**

ለማሳየት ቀላል የሆነና ከነገድ ፣ ከፖለቲካ ድርጅት ወይንም ሃይማኖት ተቋማት ጋር ያልተያያዘ በሁሉም ዜጋ ተቀባይነት ሊኖረው የሚችል የህዝባዊ እምቢተኛነት ምልክት መሰየም፣ - ለምሳሌ የተጨበጠ እጅ፣ ነጭ መሃረብ፣ ወዘተ ሊመረጥ ይችላል። እንዲሁም መሪ መፈክር ማጽደቅ ተገቢ ነው ለምሳሌ- **"በነገድ ብንለያይም አገዛዙ በሚደርስብን ስቃይ አንድ አድርጎናል፣ በአንድ ላይ እንቁም። "ማንም ነገድ በከፋፋይና ግፈኛ አገዛዝ ዘለቄታዊ ጥቅም አያገኝም።"**

**የሕዝባዊ እምቢተኝነቱ ላዕላይ አላማዎችና ግቦች፡-**

የህዝብ ንቅናቄው አገራችን ከገባችበት የፖለቲካ፣ ኢኮኖሚ፣ ሰላም ዕጦት እና ማህበራዊ ችግር በዘላቂነት የሚያወጣና ለወጣቱ ትውልድ ብሩህ ተስፋ የሚሰጥ ግብ ሊኖረው ይገባል። አገዛዙ ከወደቀ በኋላ ወደ ፍትሃዊ ማህበረሰብ የሚደረገው ሽግግር ግልፅ መሆን አለበት። **የዚህ የሕዝባዊ እምቢተኝነት መዳራሻ አገሪቱንና ቀጠናውን በሁሉም ዘርፍ አዘቅት ዉስጥ ያስገባትን አገዛዝና ከፋፋይ ስርዓቱን በማስወገድ ለኢትዮጵያዊያን ሁሉ ነጻነትን በማጎናጸፍ፣ ዘላቂነት ያለውን ሰላምን፣ በህግ የበላይነት የሚመራ የኢትዮጵያን**

**ግዛት አንድነት የጠበቀ ዲሞክራሲያዊና ፍትሃዊ ስርዓትን መገንባት ነው።** ይህ ግብ መዋቅራዊና ስርዓታዊ ለውጥ ላይ ያተኮረ ግልጽና አካታች መዳረሻ ነው። በዚም መመራት፣ ያስፈልጋል።

ምንም እንኳን የአማራው ህዝብ ከማንም የበለጠ የህልዉና አደጋ ቢያጋጥመውም፣ የሕዝባዊ እምቢተኝነቱ ሲጀመር ህዝቡ ለክፍፍል በሩን እንዳይከፍት ሁሉም ህዝብ በሚጋራዉ በደል ላይ ማትኮር ይመረጣል። የአብዛኛዉን ዜጋ ህይዎት በሚነካ ተምሳሌታዊ ድርጊት መጀመር (ለምሳሌ የነዳጅ ወይንም የማዳበሪያ ዋጋ ጭማሬን መቃወም፣ የግብር ጭማሬ ተቃዉሞ፣ የኑሮ ዉድነት፣ ጉቦኝነትና የተበላሸ አስተዳደር፣ ወዘተ)። ትግሉ በጠባብ ጥያቄዎች ልክ እንደ ጊዚያዊ የደመወዝ ጭማሬ በመሳሰሉ በሚገኙ ጊዚያዊ መልሶች መክኖ እንዳይቀር፣ አገዛዙም ይበልጥ እንዳይጠናከር እና ህዝቡ ድጋሜ ተመልሶ ወደስቃይ እንዳይገባ መጠንቀቅና ምንጊዜም ስርዓታዊ ለውጥና ላዕላይ ግቡ ላይ ማትኮር ይገባል። ተምሳሌታዊ ድርጊቱ ወይንም ጊዚያዊ ጥያቄው ግን ወደ ላዕላይ ግቡና ጥልቅ ኢፍትሃዊነትን መታገያ ስርዓታዊና መዋቅራዊ ለዉጥ ማምጣት የሚያስችል መነሻ መሆኑን መረዳት ተገቢ ነው። የሕዝባዊ እምቢተኝነቱ የአጭር ጊዜ ግቦች የሚከተሉት ናቸው፣

- በሕዝቡ ላይ የሚደረጉትን መንግስታዊ ዘር ማጥፋት፣ ጭፍጨፋዎችና ጭቆናዎችን በዘላቂነት ማስቆም፣
- የመጥፋት አደጋ የተደቀነበትን የዐማራ ህዝብ ትግል በአጋርነት መቀላቀል፣ እና
- የህዝብ ትግል የሚመሩት በተሳሳተ መንገድ ሂደው ትግሉን አንዳያደናቀፍ የተጠያቂነት ስርዓት እንዲኖር አወንታዊ ተጽዕኖ ማድረግ፣

የረጅም ጊዜ ግቦቹ ደግሞ የሚከተሉት ናቸው፣

- በሽግግር ማዕቀፍ በሚደረገው ድርድርና የስልጣን ክፍፍል የከተማው ነዋሪ በቂ ድምፅ ወይንም ወንበር እንዲኖረው በግብር አጋርነትን ለማሳሳየት፤ እንዲሁም
- የሕዝብ እምቢተኝነት ንቅናቄ የዘር አልባ አስተሳሰብን ለማጉላት እና የዴሞክራሲን ድምጽ ለማስታጋባት፣

በአጠቃለይ ሲታይና በተለያዩ አገሮች ከተደረጉት ህዝባዊ እምቢተኝነቶች የምንማረውና የኢትዮጵያን ተጨባጭ ሁኔታ ስንመዝን፣ ህዝባዊ እምቢተኛነቱ ዉጤታማ እንዲሆንና ዲሞክራሲን መገንባት እንዲቻል በአሁኑ ጊዜ የሚካሄድ ህዝባዊ እምቢተኝነት የሚከተሉት ዝርዝር መርሆች ሊከተል ይገባል።

**የሕዝብ ግንኙነትና ዲፕሎማሲ፡-**

1. **ማዕከላዊነት እና ወጥነት ያለው አመራርና መልዕክት እንዲኖር ማድረግ የግድ ያስፈልጋል፡-**

ማዕከላዊነት ካለው ህዝባዊ እምቢተኝነቱን ከሚያስተባብረው ድርጅት/ስብስብ የሚተላለፉ መልዕክቶችን፣ መግለጫዎችን፣ የድርጊት መርሃግብሮችን፣ መመሪያዎችን፣ የስነምግባር ደንቦችንና ዝርዝር ስትራቴጂዎችን ሚዲያዎችም ሆነ ተባባሪ ድርጅቶች በልዩ ጥንቃቄ ሳያዛቡ እንዲያስተላልፉ ማድረግ ተገቢ ነው። በማህበራዊ

ሚዲያ የሚደረጉ ዘመቻዎች ከሚያስተባብረው ድርጅት/ስብስብ ተለይተው በሚቀርቡ የየወቅቱ የትኩረት ጉዳዮች ላይ እንዲሆኑ ማድረግ፣ እንዲሁም ዘመቻውን ድርጅቱ በሚሰጠው መመሪያ መሰረት ማከናወን ይገባል። የሚያስተባብረው ድርጅት/ስብስብ ያቅዳል፣ ያደራጃል፣ ገንዘብና ባለሙያ ያሰባስባል፣ አስተባብሮ ያስፈጽማል እንዲሁም ሂደቱን እየገመገመ ዝርዝር ስትራቴጂውንና ታክቲኩን ያወጣል ያስተካክላል። የድርጅት አስፈላጊነት ቁልፍ በመሆኑ ከምንም ነገር በላይ ቅድሚያ ሊታሰብበት ይገባል። ድርጅቱ አካታች እንዲሆንና በማህበራዊ ሚዲያው ዘመቻ ሊረዱ የሚችሉ፣ የፖሊሲ፣ የተግባቦት፣ የስትራተጂ፣ የስነልቦና፣ የኢንተርነት ሴኩሪቲ አይነት ባላሙያዎችን የሚያካትት ቢሆን ይመርጣል።

2. **የብዙሃን መገናኛዎች በቅንብር እንዲሰሩ ማድረግ፡-**

በብዙሃን መገናኛዎች (ህበራዊ ሚዲያ፣ ገለልተኛ ሚዲያና እና የተለያዩ የግንኙነት ዘዴዎችን መጠቀም) የሕዝባዊ እምቢተኝነቱን ራዕይ፣ መልዕክት እና ስትራቴጂ አንድ ወጥና ለህዝቡ ግልጽ በሆነ መንገድ ማስተላለፍ ያስፈልጋል። የሚተላለፉ መልዕክቶች ሁሉ ተዓማኒ፣ አካታች መሆናቸውን፣ በጥንቃቄ የተዘጋጁ አንድነት ላይ ያተኮሩና በነገዶች መካካል፣ እንዲሁም ለህልዉና በሚታገሉ መካካል ቅሬታንና ክፍፍልን የማያስነሱና ምንጊዜም ዋናው የሕዝባዊ እምቢተኝነቱ ግብ ላይ ያተኮሩ መሆናቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። እንዲሁም የትግሉ ደጋፊ ብዙሃን መገናኛዎች፣ የጋራና የተቀነባበረ አሰራር እንዲኖራቸው፣ የጎንዮሽ ትግል እንዳያደርጉ፣ አንድ የጋራ ስብስብ (ኮንሶርቲየም) እንዲኖረቸው ማድረግ ይጠቅማል። ይህም በጋራ ጉዳዮች ላይ ተባብረው እንዲሰሩ፣ የጋራ የስነምግባር ደንብ እንዲኖራቸው፣ እንዲሁም በጋራ ገንዘብ እንዲያሰባስቡ ይረዳቸዋል። ተቀናጅተው ህዝባዊ እምቢተኛነቱ ላዕላይ ግብ ላይ እንዲያተኩሩ ማድረግ ተገቢ ነው። ቢቻል ህዝባዊ እምቢተኝነቱ የሚመራው የራሱ ሚዲያና ቃል አቀባይ ቢኖረው ይመረጣል።

3. **አጠቃላይ ህዝቡን ማንቃት፡-**

ከሚያስተባብረው ድርጅት/ስብስብ በሚሰጠው መመሪያና የትኩረት ነጥቦች መሰረት ለአጠቃላይ ህዝቡ የሕዝባዊ እምቢተኝነት ግብ፣ የሚያወጣው ስትራቴጂና የጥንቃቄ ትምህርቶችን በብዙሃን መገናኛዎች ማስተማር ያስፈልጋል። ወደ 35 አመታት ዘረኝነትን፣ ክፍፍልንና ጥላቻን የተሰበከን ህዝብ ስለአንድነትና ትብብር ስለጋራ አገራዊ ጥቅም ማስተማር ከባድና ፈታኝ ስራ እነደሚሆን መገንዘብ ያስፈልጋል። ገዢው መንግስት በህዝብ ላይ እያደረሰ ያለውን ጉዳት በተጨባጭና አሃዛዊ ማስረጃ በባለሙያ ማቅረብ፣ በአግባቡ መሰነድ፣ ህዝቡንም ሆነ የአለም-አቀፍ ማህበረሰቡን ለማሰመን ይረዳል።

4. **በትግሉ የሞራል የበላይነትና ግልጽነት መያዝ፡-**

ስለ ነዉጥ አልባ ህዝባዊ እምቢተኛነት ማስተማር፤ የሕዝባዊ እምቢተኝነቱን ሥነ ምግባር ከፍ ያለ ቦታ እንዲይዝ በማድረግ፣ በአገርም ዉስጥ ሆነ በዉጭ አገር ሰፊ ድጋፍ ለማግኘት እና የአገዛዙን አስከፊነት ዘር ለማጥፋት ያደረገዉን ሁሉ በማስረጃ በማሳየት በቀላሉ ማስረዳት ይጠቅማል። ዘር ማጥፋት እየፈጸመ ላለው አገዛዝ ሰበብ ከመስጠት መቆጠብና ሰላማዊ ያልሆኑ ዘዴዎችን አለመጠቀም፣ **ደጋፊን ማብዛትና ጠላትን መቀነስ ቁልፍ መርህ ነው።** ለትግሉ አስተዋጾ ማድረግ የሚችሉትን ሁሉ በጥንቃቄ በሚያስፈልጉበት ቦታ ሁኔታና ጊዜ መጠቅም እንጂ ደጋፊዎችን መግፋት ትግሉን ይጎዳል፡፡

5. **የተመሰጠሩ የመልዕክት መላላኪያ መተግበሪያዎችን መጠቀም፡-**

ማህበራዊ ሚዲያ እና ኢንተርኔት (ተደራሽ ከሆነ)፡ ለማደራጀት እና ለመገናኘት የተመሰጠሩ (encrypted) የመልእክት መላላኪያ መተግበሪያዎችን (ለምሳሌ፡ ሲግናል፣ ቴሌግራም) ይጠቀሙ። እንደ ትዊተር፣ ፌስቡክ እና ቲክ-ቶክ ኢንስታግራም ያሉ መድረኮች፣ መልዕክቶችን በፍጥነት የማጉላት ችሎታቸው፣ የእንቅስቃሴውን መልእክት ለማሰራጨት ውጤታማ መሳሪያዎች ሊሆኑ ይችላሉ። የቴክኖሎጂ አማራጮች፡ የበይነመረብ ተደራሽነት በጣም የተገደበ ከሆነ እንደ በራሪ ጽሑፎች፣ ሰው በሰው መልዕክቶችን መጠቀም፡ ይረዳል። ስብሰባዎች ቢቻል ሚስጥራዊና ደህንነታቸው የተጠበቀ መሆን አለበት።

6. **የገዥዉን አካል አባላት ማሳመንና ማስከዳት፡-**

ደጋፊን ማብዛት ጠላትን መቀነስ የሚለውን መርህ በመከተል፣ በገዥው አካል ውስጥ ለዘብተኛ ወይንም ምክንያታዊ የሆኑትን ወይንም በትንሽ ጥቅም የተደለሉና የተሳሳቱ ግለሰቦች ሊኖሩ እንደሚችሉ መገንዘብና እነርሱን በማሳመን በአመራሩ ላይ ተስፋ እንዲቆርጡና እና ከተገፋው ህዝብና ወገናቸው ጎን እንዲሰለፉ ደጋግሞ ማስተማር፣ ወይንም ቅስቀሳ ማድረግ ትኩረት ይሻል። በጠላት መካከል ክፍፍል እንዲደርግ ስልት አዘጋጅቶ በማስረጃ ላይ ተመርኩዞ ስራ መስራት ይገባል።

7. **መንግስት የሚፈጽማቸውን ዘር ማጥፋት፣ ሰቆቃዎች፣ ግድያዎች፣ ማፈናቀሎችና ሌሎች ሰብዓዊ መብት ረገጣዎችን በአግባቡ መሰንድና ማጋለጥና ገዢዎቹን ተጠያቂ ለማድረግ መዘጋጀት፡-**

ማስረጃዎችን ለመያዝና ለመሰነድ ዲጂታል መሳሪያዎችን መጠቀም እና ወደፊት አለማቀፍ ምርመራ እና ተጠያቂነት እንዲኖር በስፋት መዘጋጀት ይገባል። ትግሉን ሰብአዊ ለማድረግ እና በአገር ውስጥም ሆነ በአለም አቀፍ ደረጃ አዘኔታንና ድጋፍ ለማግኘት በአገዛዙ ስር የሚሰቃዩትን ግለሰቦች ግላዊ ታሪኮችን እና ምስክርነቶችን ሰንዶ በተለያየ ሚዲያ ለህዝብ ማሳወቅ፣ ተርጉሞ ለአለም አቀፍ ማህበርሰብ ማሳወቅ። የሰብአዊ መብቶች ሪፖርት፡ የአገዛዙን ጭቆናና የዘር ማጥፋት የሚያሳዩ ተጨባጭ ምስክሮችን፣ ፎቶዎችን እና ቪዲዮዎችን ለአለም አቀፍ ድርጅቶች ማካፈል። ሁኔታውን እንዲዘግቡ ዓለም አቀፍ ጋዜጠኞችን ማበረታታት። ለዚህም ይረዳ ዘንድ የተማከለና በሙያ የሚመራና ብቃት ያለው የዉጭ ቋንቋ ችሎታ ያለው ቃል አቀባይ መፍጠር።

8. **አለም አቀፋዊ ተጽዕኖን መቋቋም የሚያስችል ስልት ማዉጣትና ድጋፍ መጠየቅ፡--**

ወቅቱንና የአገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ አለም አቀፋዊ ተጽዕኖወችን ከግምት ዉስጥ ያስገባ የህዝባዊ እምቢተኛነትና የዲፕሎማሲ ስልት መንደፍ። ከዉጭ ሊመጣ የሚችልን ተጽዕኖ መተንበይና የህዝባዊ እምቢተኛነቱ እንዳይጨናገፍ እንዲሁም አለማቀፋዊ ድጋፍ እንዲያገኝ በጥንቃቄ የተዘጋጀ የዲፕሎማሲና የህዝብ ግንኙነት ስራ መስራት። አለም አቀፍ የግንዛቤ ማስጨበጫ ዘመቻዎችን በማህበራዊ ሚዲያም ሆነ በአካል በመገኘት፣ ሰልፍ ማድረግ። ትግሉን ለማጉላት እና የአገዛዙን አፋኝ እርምጃዎች ጨካኝነት፣ ዘር ማጥፋትና ዘር ማጽዳት የመሳሰሉት ትኩረት እንዲያገኙ አለም አቀፍ መድረኮችን መጠቀም። ከዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች፣ የተባበሩት መንግስታት አካላት፣ አለማቀፍ ሚዲያ እና ለሰብዓዊ መብት ድርጅቶችና ጆሮ ለሚሰጡ መንግስታት ማሳዎቅ። በገዥው አካል ላይ ማዕቀብ፣ ዲፕሎማሲያዊ ማግለል እና ሌሎች የውጭ መንግስታት ሊያደርጉ የሚችሏቸውን እገዳዎች እንዲያደርጉ መጠየቅ።

9. **የተመረጠ ማዕቀብ እንዲደረግ መጠየቅ፡-**

አገዛዙን እያስቀጠሉ ያሉ የአገዛዙ ባለስልጣናት፣ የመንግስት ኩባንያዎች ወይም የውጭ ኩባንያዎች ወይንም አገዛዙን መሳሪያ የሚያስታጥቁ አገሮች ላይ አለም አቀፍ ማዕቀብ እንዲጣል ማበረታታት። ማዕቀቡ በአገር ዉስጥ እንደ ነዳጅ፣ መከላከያ፣ አየር መንገድ፣ ንግድ ባንክ፣ ኢትዮ ቴሌ ወይም ፋይናንስ ያሉ ቁልፍ ዘርፎች ላይ ሊያተኩር ይችላል። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣ በውጭ ያሉ ኢትዮጵያዊያን ከዉጭ ወደ ኢትዮጵያ ገንዘብ እንዳይልኩ ማድረግ።

**የእምቢተኝነቱ የትግል ዘርፍ ተግባራትና ትኩረት፦**

**፩) የሕዝባዊ እምቢተኝነቱን ግንባር-ቀደም ችግሩን በተጋፈጡት አማራ ከተሞችና አማራዎች በሚበዙባቸው ከክልል ውጭ ከተሞችና አካባቢዎች መጀመር ግድ ይላል።** ሰላማዊ ሰልፎች በዋና ዋና ከተሞች በመጀመር ሰፊ ተቃውሞዎችን እና የስራ ማቆም አድማዎችን በአጠቃላይ አገሪቱ ማስፋፋት፣ ሌሎችም የአገሪቱ ክፍሎች ትግሉን እንዲቀላቀሉ በግልጽ ጥሪ ማቅረብ። ተቃዉሞዎች ሰላማዊ እና በነገዶች መካከል አንድነትን የሚያሳዩ መሆን አለባቸው። የሚያዙት መፈክሮች በጥንቃቄ የተመረጡና በአዘጋጁ የተፈቀዱ የትግሉን ላዕላይ ግብ የሚያሳኩ ብቻ መሆን አለባቸው። በነዚህም ሰልፎች፣ ከብዙ በጥቂቱ፣ የሚከተሉትን መጠየቅተገቢ ነው፦

1) በነገድ ብንለያይም በመንግስት በሚደርስብን ስቃይ አንድ ነን፣
2) የፖለቲካ እስረኞች በአስቸኳይ ይፈቱ፣
3) በተለያየ የአገሪቱ አካባቢዎች በሰላማዊ ሰዎች ላይ አገዛዙ የሚፈጽመዉን ወንጀል ያቁም፤
4) በአማራ ላይ በአገዛዙ እየተፈጸመ ያለው ዘር ማጥፋት ይቁም፣
5) አገዛዙ በህዝብ ላይ የሚደረገውን ማፈናቀል ያቁም፣
6) ነዋሪዎችን/ዜጎችን በማፈናቀል መሬትን መሸጥ ይቁም፣
7) መሬትን ለውጭ ዜጎች ለመሸጥ የሚደረገው ዝግጅት ይቁም፣
8) አገዛዙህዝብን በህዝብ ላይ ማነሳሳቱን ያቁም፣
9) ለሚጨፈጭፈን መንግስት ግብር አንከፍልም፣
10) አፋኝ ህጎች ይወገዱ፣
11) በገዥው አካል ላይ አለም አቀፍ ጫናዎች ይደረጉ፤
12) ህዝብን የጨፈጨፉ ባለስልጣናትና የጦር መሪዎች ለፍርድ ይቅረቡ፣
13) በአማራና ትግራይ ህዝብ ላይ ዘር ማጥፋት የፈጸመው አቢይ አህመድ ለፍርድ ይቅረብ፣
14) ከፋፋዩና ህዝብ ጨፍጫፊው መንግስት ከስልጣን ይውረድ፣
15) የመከላከያ ሃይልና የአካባቢ አድማ በታኝ ሚሊሻ ወደጨፍጫፊው መንግስት መሳሪያህን አዙር፣ ከድሃው ወገንህ ጋር ቁም፣
16) ለጊዜያዊ ጥቅም ተገዝታችሁ ከገዢው መንግስት ጋር ያበራችሁ ካድሬዎች ከወገናችሁ ጋር ቁሙ፣
17) አገዛዙ በብልሹ አመራሩ የፈጠረውን ረሃብና የኢኮኖሚ ድቀትና የኑሮ ዉድነት ያቁም፣
18) ራብን፣ የሰራተኞች ደመዎዝ በአስቸኳይ ይጨመር፣
19) ተመጣጣኝ ደመወዝ እስኪጨመር አጠቃላይ ስራ ይቁም፣

20) መኖር አልቻልንም፣ የነዳጅና የማደበሪያን ሌሎች ቁሳቁሶች ዋጋ ይቀነስ፣

21) ስራ አጥነት ያብቃ፤

22)ባላሙያዎች በክልል ወይም ነገድ ሳንከፋፈል ለመብታችን በአንድነት እንነሳ፣

23) የአገር ሃብት የመዘበሩ ባለስልጣናት ለፍርድ ይቅረቡ፣

24) እድሚያቸው ያልደረሰ ህጻናትን እያፈኑ ወደ ጦር ሜዳ መማገድ ይቁም፣

25) በእምነት ተቋማት ላይ የሚደረገው መከፋፈልና አፈና ይቁም፣

26) በቤተክርሲያን ላይ የሚደረገው አፈና ይቁም፣

27) የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አባቶች ግድያ ይቁም፣ ገድዮች ለፍርድ ይቅረቡ፣

28) መንግስት በየአቅጣጫው የሚያደረገውን ጠብ አጫሪነት እርስ በርስ ማጋጨት ያቁም።

፪) **የመንግስት ተቋማትን 'ቦይኮት' ማድረግ፡-** ማዕከላዊነት ካለው ህዝባዊ እምቢተኝነቱን ከሚያስተባብረው ድርጅት/ስብስብ በሚሰጥ ዝርዝር መመሪያ መሰረት፣ በመንግስት ቁጥጥር ስር ያሉና አምባገነኑን መንግስት ለማስቀጠል እየረዱ ያሉ እንደ ንግድ ባንክ፣ ኢትዮ ቴሌ፣ ኢትዮጵያ አየር መንገድ የንግድ ድርጅቶችን፣ የህዝብ አገልግሎቶችን ወይም የፍጆታ እቃዎችን በአገር አቀፍ ደረጃ ወይም በክልል ደረጃ በደራጃ ቦይኮት ማድረግ ማስተባበር። የገዢዉን መንግስትን ስራ ማወክ፣ ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግ ሌሎች የመሳሰሉ ዘዴዎችን መጠቀም ይቻላል። ሠራተኞችን በማደራጀት የሥራ ማቆም አድማ ወይም መቀዛቀዝ እንዲያደርጉ ዋና ዋና የኢኮኖሚ ዘርፎችን በተለይም ወሳኝ በሆኑ ኢንዱስትሪዎች ወይም በመንግሥት ተቋማት ውስጥ እንዲሰማሩ ማድረግ ያስፈልጋል።

፫) **ስራ ማቆም መጥራት የእምነት ተቋማት አድማ መጥራት፡-** የአገዛዙን ስልጣን ለማራዘም የሚያገለግሉና በመንግስት ታማኝ ካድሬዎች የሚመሩ የመንግስት ዩኒቨርሲቲና ትምህርት ቤቶችን ወይም ዩኒቨርሲቲዎችን ትምህርታቸውን እንዲያቆሙ ማበረታታት። የመንግስት የፖለቲካ ሹመኞች ከስልጣን እንዲወርዱ በሰልፍ መጠየቅ፣ ታክሲዎች የትራንስፖርት አገልግሎትም እንዲሁም የሃይማኖት ተቋማትም ህዝቡ መንግስት እንዲውርድ እንዲታገል ማበረታት አለባቸው። እንዲሁም ህዝቡ በተውሰነ ሰዓት፣ ጸጥ በሚል ምሽት፣ በየቤቱ በር ላይ ወጥቶ እግዚኦ ማለት፣ ቤተክስቲያኖች ደውል እንዲደዉሉ ማድረግ፣ ወደ እምነት ተቋማትም ከሄዱ ጥቁር ልብስ ለብሶ መሄድ፣ የጸሎት ስርዓቱ ሲያበቃ መንግስት ይዉርድ ብሎ መጮህ፣ የመሳሰሉትን ማድረግ። በእምነት ድርጅቶች ላይ ተጽዕኖውና አፈናው በመቃወም ለተወሰኑ ቀናት በቤት ዉስጥ ተወስኖ የመጸለይና ከእምነት ተቋማት በመቅረት አድማ መጥራት፣ ሚዲያን ማሳወቅና የገዢዉን መንግስት ወንጀል በዚህ መንገድ ለአለም አቀፉ ማህበረሰብ ማጋላጥ።

፬) **መንግስትን አለመታዘዝ፡-** በመንግስት ለተለያየ አገልግሎት ለመመዝገብ ፈቃደኛ አለመሆን፣ ግብር አለመክፈል፣ የመብራት የዉሃ ክፍያ አለመክፈል፣ ወይም ሌሎች የመንግስት ታዛዥነትን አለመቀበል ያሉ ኢፍትሃዊ ህጎችን አለማክበር። ከዚህ መንግስት መሬት በሊዝ አለመግዛት፤ ከዚህ መንግስት ጋር ተባብረው የአገር ሃብት የሚመዘብሩ ነጋዴዎችን ለይቶ ማወቅና ማጋለጥ፣ አስገዳጅ ሁኔታ ከሌለ በስተቀር ገንዘብ ከውጭ ወደ ኢትዮጵያ አለመላክ፣ በዉጭ ያሉ ኢትዮጵያዊያን ቢጫ ካርድ አለማዉጣት፣

**፰) አማራጭና ጊዚያዊ የትይዩ የአገልግሎት የአስተዳደር ስርዓቶችን መመስረት፡-** እንቅስቃሴው ሲበረታ ስራ እንዳይተጓጎልና ህዝብ እንዳይጎዳና እንዳይማረር በአገዛዙ ሙሉ በሙሉ ቁጥጥር ባልተደረገባቸው አካባቢዎች አማራጭ የአስተዳደር ዘዴ ማደራጀት ያስፈልጋል። ይህ አማራጭ ጊዚያዊ አስተዳደር በከፍተኛ ዲሲፕሊን የሚመራና በህዝብ ተቀባይነት ባላቸው/ አረጋዊያን/ ሰዎች የሚመራ ይሆናል። እንዲሁም ህዝቡ እንደ ትምህርት፣ ጤና አገልግሎት፣ እና ትራንስፖርት፣ ጸጥታ እጦት እንዳይማረርና ተስፋ እንዲኖረው ትይዩ ተቋማትን ለምሳሌ- አማራጭ የትምህርት ሥርዓቶችን/ታላላቆች ታናናሾቻቸዉን በየሰፈሩ የሚያስተምሩበት ወይንም የሚይስጠኑበት የተማረ ያስተምር ዘመቻ/ ፣ የጤና አገልግሎቶችን፣ እና ከአገዛዙ ነጻ ሆነው የሚሰሩ ጸጥታ አስከባሪዎች መመደብ፣ ለባንኮችና ጤና አግልግሎቶች ለመሳሰሉት ጥበቃ ማድረግ ይገባል።

**፱) የመንግስት ክትትልን በጥንቃቄ ማየት፡-** ከመንግስት ክትትል፣ አፈናና ግድያ ለመዳን ሚስጠራዊና፣ በከፍተኛ ዲሲፒሊን የሚመራ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ (ሴኩር) ግንኙነቶችን እና ድብቅ የግንኙነት መረቦችንና ዘዴዎችን መጠቀም፣ አክቲቪስቶች በግል የደህንነት እርምጃዎች የሰለጠኑ መሆናቸውን ማረጋገጥ። ለዚህም የኢንተርኔት ሴኩሪቲና ቴክኖሎጂ አዋቂዎችን ምክር መጠቀም ያስፈልጋል። በተዝረከረከ፣ ባልተማከለና ልቅ በሆነ መንገድና ባልታረመ ቋንቋ መረጃም ሆነ መግለጫ ማዉጣት ትግሉን ይጎዳል፣ ክፍፍል ይፈጥራል ደጋፊዎችንም ይበትናል። የሚተላለፉ መልዕክቶች እጥር ምጥን ያሉና በጥንቃቄ የተዘጋጁ መሆን አለባቸው።

**፲) በፖለቲካና በእምቢተኝነቱ ምክንያት ለሚታሰሩ እስረኞች ተገቢውን ድጋፍ ማድረግ፡-** ለሚታሰሩ የሕዝባዊ እምቢተኝነቱ መሪዎች፣ ተሳታፊዎችና አንቂዎች የገንዘብ፣ የህግ እና የቁሳቁስ ድጋፍ ለመስጠት ኔትወርኮችን መፍጠር። የአካባቢው ማህበረሰብ ተቃውሞ እንዲያዘጋጁ፣ ገንዘብ እንዲያሰበስቡ፣ መልዕክት እንዲያስተላልፉ እና የታሰሩ አንቂዎችን ቤተሰቦች እንዲደግፉ ማድረግ። የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት፣ መስጊዶች እና የማህበረሰብ ማዕከላት በማዳረስ ጥረቶች ውስጥ ቁልፍ አጋሮች ሊሆኑ ይችላሉ። በአገዛዙ ላይ ጫና በመፍጠር እንዲፈቱ ዘመቻ ማካሄድ፣

**፲፩) ለሚሰደዱ የትግሉ መሪዎች ከለላ መፈለግ፡-** ለአንቂዎችና፡- ለትግሉ መሪዎች አለምአቀፍ ጥበቃን መፈለግ ተገቢ ይሆናል። በግዞት ሊሰደዱ የሚችሉ ለአንቂዎችና የትግሉን መሪዎች ለመርዳት መዘጋጀት፣

**፲፪) የትግል መዝሙር እና ባህላዊ እሴቶችን በመጠቀም ትግሉን ማፋፋም፡-** የየአካባቢዉን ሙዚቃ፣ ጥበብና፣ ስላቅን በመጠቀም ህዝቡን በመቀስቀስ የጋራ ማንነት እና የባህል ስሜትን በማጎልበት ለትግል ማነሳሳት፣ ጨፍጫፊውን መንግስት ለመቃወምና ለመጣል መጠቀም ያስፈልጋል።

**፲፫) ምንጊዜም ከጊዜው ቦታውና ሁኔታው ጋር የሚጣጣም ስትራቴጂ ያስፈልጋል፡-** ይህ ስትራቴጂ በየጊዜው ከሚለዋወጠው ሁኔታና የአምባገነኑ መንግስት ተለዋዋጭ ባህሪን በመረዳትና የሕዝባዊ እምቢተኝነቱ የሚመራው ማዕከል እንደየተጨባጭ ሁኔታው ሊያሻሽልና ሊያጠናከረው ይገባል። እንዲሁም ዝርዝር የተግባር መመሪያና ታክቲክ ሊያወጣለት ይገባል።

<u>የጸደቀበት ቀን፡-</u> **ነሃሴ 29, 2017 ዓ. ም**